ለኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው

አዲስ አበባ

ጉዳዩ   ርክክብ እንዲፈጸም ስለመጠየቅ

ከመስፍን ወልደ ማርያም፣ ምክትል ሊቀ መንበር

የአንድነት ፕሮግራም በመግቢያው መጀመርያ ላይ ‹‹ዕውነተኛ የወገን ፍቅርና ምክንያታዊ አስተሳሰብ ካለ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው እየተሸጋገረ ለዘመናት አብረውን የኖሩና እየተወሳሰቡ የመጡ ፈርጀ ብዙ ችግሮቻችንን እንፈታቸዋለን የሚል እምነት አለን›› ይላል፡፡

ይህን በፕሮግራሙ ያሰፈረን ፓርቲ የሚመሩ ግለሰቦች ሃገራዊ ችግርን ቀርቶ የፓርቲን ውስጣዊ ችግር ለመፍታት ፈቃደኝነት አጥተው፣ለህግ ከመገዛት ይልቅ የፖለቲካ ውሳኔን በመምረጣቸው አንድነትን ለከፋ አደጋ ዳርገውታል፡፡

ይህን አደጋ በመታደግ የአንድነትን ህልውና ማስቀጠል የሚቻለው የፓርቲው ከፍተኛ የሥልጣን አካል የሆነው ጠቅላላ ጉባኤ ብቻ በመሆኑ በመተዳደርያ ደንቡ መሠረት በ1/3ኛ አባላት በተጠራው የሚያዝያ 10/2002 ልዩ ጉባኤ ላይ በመገኘት አንድነትን የማዳኑን መፍትሔ በጋራ እንድንፈልግ የቀረበላችሁን ጥሪ አልተቀበላችሁም፡፡

የፓርቲው ህልውና አደጋ ላይ መሆን ያሳሰባቸው የጉባኤ አባላት ግን ጥሪውን ተቀብለው ከአብዛኛው የሃገሪቱ ክፍል በመምጣት ባካሄዱት ልዩ ጉባኤ ውሳኔዎችን አሳልፈዋል፡፡የደንብ ማሻሻል አድርገው አዲስ የምክር ቤት አባላት መርጠዋል፡፡

ስለሆነም አረካካቢ ኮሚቴ በማቋቋም፣ የፓርቲውን ሕጋዊነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ ማህተም፣ፅ/ቤት፣ሰነዶችና ንብረቶች ርክክብ በመፈጸም የጉባኤውን ውሳኔ ተፈጻሚ እንዲያደርጉ እያሳሰብን፣ ከዚህ ቀን ጀምሮ በፓርቲው ማሕተም በመጠቀም፣የምታደርጉት እንቅሳቀሴ ሁሉ የፓርቲውን ደንብና የሀገሪቱን ህግ የሚጻረር እንዲሁም የጉባኤውን ውሳኔ የሚጥስ መሆኑን እናስታወቃለን፡፡

<u>እንዲያውቁት፡-</u>

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

አዲስ አበባ፡፡

ለቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፖሊስ፣ አዲስ አበባ

ሚያዝያ 18 ቀን/2002 ዓ/ም